## የመኢአድን ድጋፍ በአውሮፓ ስለ ማደራጀት፤ የእንሰባሰብና: የእናሰባሰብ: መልዕክት/ ጥሪ::

መኢአድ: ከቅንጅት: መመሥረት: በፊት: በተጠናከረ: ሁኔታ: ይንቀሳቀስ: የነበር: ሰፊ: መሠረት ያለው ሃገር አቀፍና ሕብረ ብሄራዊ ድርጅት እንደነበር የተረጋገጠ ሃቅ ነው:: ቅንጅት በተቋቋመበት ጊዜም መሠረትና ግንብ ሆኖ ሕብረትና ውህደቱ በአጭር ጊዜ በእግሩ እንዲቆም በማድረግ ሌሎቹ ድርጅቶች ካደረጉት የላቀ አስተዋጽኦ አድርጓል::

በቅንጅት መሪዎቸ መካከል መለያየት ከተፈጠረ በኋላ ሌሎች የቅንጅት መሥራች አባሎች የኢትዮጵን ሕዝብ ለዘላቂ ሰላምና ብልጽጋና ለማብቃት የተቀየሰውን የትግል ስልት ለውጠው አዳዲስ ስም መርጠው ወደተለያየ አቅጣጫ ሄደዋል:: መኢአድ ግን የገዥው ፓርቲ ቅንጅት የሚለውን ስሙን በጉልበት ነጥቆ ለሌላ ስለሰጠ አማራጭ በማጣት የቀድሞ ስሙን ይዞ ሃገር አቀፍና ሕብረብሔር አቋሙን አጠናክሮ በመላ ኢትዮጵያ ሕዝብ መካከል በመንቀሳቀስ ላይ ነው::

መኢአድ በመላው ኢትዮጵያ ተጠናክሮ እየተንቀሳቀሰ እያለ ከአውሮፓ ደጋፊዎች የሚያገኘው ድጋፍ ግን ከቀድሞው አንጻር ሲታይ ድክመት ይታይበታል:: የዚህ የእንሰባሰብና የእናሰባስብ መልእክት ዋናው አላማ በአውሮፓ ያለውን የመኢአድ የድጋፍ እንቅስቃሴ ለማጠናከር ነው::

ከቅንጅት መቋቋም በኋላ፣ በአውሮፓ በሰፊው ተደራጅቶ ይንቀሳቀስ የነበረው የድጋፍ ድርጅት በሙሉ መኢአድ በሰጠው መመሪያ መሠረት ለቅንጅት ድጋፍ ሲያደርግ መቆየቱ ይታወቃል:: የቅንጅት አመራር ከታሰረ በኋላ ደግሞ ለማስፈታት ያልታከተና ውጤታማ የሆነ እንቅስቃሴ አድርጓል:: መሪዎቹ ከተፈቱና የቅንጅት አመራር ከተከፋፈለ በኋላ ግን በአውሮፓ የሚገኘው የመኢአድ ድጋፍ በአገር ውስጥ ለሚደረገው ሠላማዊ ትግል የሚአደርገው ድጋፍ አቅም ያነሰው ሆኖ ታይቷል:: ስለሆነም በአውሮፓ አገሮች የምንገኝ የመኢአድ ደጋፊዎች በመሰባሰብና በማሰባሰብ የመኢአድ ራዕይ በአውሮፓ የነበረውን ቦታ እንዲይዝ ደጋፊዎቹ በያለንበት ከተማና አገር እየተደራጀንና ድርጅታዊ መረባችንን እያስተሳሰርን እንድንቀሳቀስ ጥሪ እናቀርባለን::

ይህ የመሰባሰብና የማሰባሰብ ጥረት መደረግ ያለበት በየከተማውና በየአገሩ ባላችሁ የመኢአድ ደጋፊዎችና አገር ወዳዶች ሆኖ አካሄዱ ደግሞ አቀራራቢና አሰባሳቢ መሆን ይኖርበታል:: ከሁሉም በላይ ደግሞ በደጋፊው ጥረት ከሥር የሚነሳና እድገቱን ጠብቆ፣ አላማውን አውቆ፣ በአውሮፓ ደረጃ መዋቀር የሚችል የድጋፍ እንቅስቃሴ በድጋሚ እንድንፈጥር እንድንተባበርና እንድናስተባብር ጥሪ እናደርጋለን::

እስከአሁን በተለያየ መልኩ ለመኢአድ ድጋፍ የሚሰጡ በስዊድንና ፣ በእንግሊዝ፣ በድርጅት መልኩ፤ በሆላንድ፣ በኖርዌይና በጀርመን ደግሞ በቡድንና በግለሰብ ደረጃ መኢአድን እየደገፉ ይገኛሉ። ድርጅት ሃይል ነውና በአውሮፓ ተበትኖ ያለው የመ.ኢ.አ.ድ. ደጋፊ ሁሉ፤ ድርጅት በሌለባቸው ሃገሮች ለመደራጀት፤ ድርጅት ባሉበት ሃገር ደግሞ ለመጠናከር ደጋፊዎች ሁሉ እየተሰባሰባችሁና እያሰባሰባችሁ የአውሮፓውን የድጋፍ ድርጅት ምስረታ ለማመቻቸት ከዚህ በታች በተመላከቱት አድራሻዎች ግነኙነት እንድትፈጥሩ ጥሪያችንን እናቀርባለን::

ለመብታችን፣ ለሕዝባችን ደህንነትና አንድነት አብረን እንቁም::
ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር !!!!

**Contacts: - Sweden: - demere.hm@telia.com**
**United Kingdom: - aeupdigafuk@yahoo.co.uk**

EthioLion.com